# ኢ ሕ አ ፓ በ ቶ ሮ ን ቶ

በቶሮንቶ ካናዳ የኢሕአፓ ደጋፊዎች ያዘጋጁት የእራት ምሽት ፕሮግራም ባለፈው ማርች 19/2011 በላሊበላ ሬስቶራንት ከተጠበቀው በላይ ስኬታማ ሆኖ ተከናውኗል። የዝግጅቱ ዓላማ በከተማዋና አካባቢው ኑዋሪ ለሆኑና የሀገራቸው ጉዳይ ከልብ አሳስቡዋቸው ላለፉት በዛ ያሉ ዓመታት በሚያመቹዋቸው ልዩ ልዩ መንገዶች ተቀራርበው በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ትግል አስተዋጻኦ ሲያደርጉ ለቆዩ ወገኖች ስለፓርቲውና ተጨባጩ የኢትዮጵያና ዓለም አቀፍ ሁኔታ ገለጻ ለመስጠት ነበር።

ከእራት ግብዣው ሥነ ሥርዓትት በሁዋላ፣ በዕለቱ የተካሄደው ውይይት የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል አቶ ፋሲካ በለጠ በስልክ ባደረጉት ሰፋ ያለ ገለፃ የጀመረ ሲሆን፣ ከገለፃው በሁዋላ ከዝግጅቱ ተሳታፊዎች ለቀረቡት በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች አጥጋቢ መልስና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

አቶ ፋሲካ በመግለጫቸው ሰሜናዊው የአፍሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ በለውጥና በአብዮት ማዕበል እየተዋጠ ባለበትና ይህም የለውጥ ጅረት ግፍና መከራ ከየትኛውም የዓለማችን ክፍል በከፋ መልኩ በሚካሄድባት ሀገራችን ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ በመዳሰስ ለዚህ አይቀሬ ለሆነው የሕዝብ አመፅ በሁለንተናዊ መልኩ መዘጋጀት የታጋይ ደርጅቶች ሁሉ የወቅቱ ሀላፊነት መሆኑን አስገንዝበዋል። በመቀጠልም ፈርጀ ብዙ የሆነው የሀገራችን ችግር የሁሉንም የፖለቲካ ደርጅቶችና ሰብስቦችን የተባበረ ጥረት እንደሚጠይቅና ባንድ ድርጅት የተናጠል ትግል የምንመኘውን ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል አስገንዝበዋል።

ይህን በተመለከተ ኢህአፓ በሁሉም መስክ ህዝቡን በመቀስቀስና በማደራጀት ከመቼውም በላቀ ሁኔታ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል። ከሁሉም በላይ የትግሉ ዋነኛ መድረክ በሆነው በሀገራችን መሬት ላይ ሕዝቡን በተለይም ወጣቱን ማደራጀት ለትግሉ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ የኢሕ አፓ ወጣት ክንድ (ኢወክንድ) ወጣቱን የማሰባሰብ ተግባሩን በሰፊው የተያያዘው መሆኑንንም አስምረውበታል።

በመጨረሻም፣ ዛሬም እንደትላንቱ ኢሕአፓ የሚያካሂደውን ትግል ለመደገፍና ለመከታተል ጊዜያቸውን ሰውተው በቦታው የተገኙትን ወገኖች በራሳቸውና በድርጅታቸው ስም አመስግነው ይህ አይነቱ መቀራረብና መረዳዳት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል። ወቅቱ የተፋፋመ ትግል የሚካሄድበት ጊዜ መሆኑን ያስገነዘቡት አቶ ፋሲካ፣ ኢሕአፓ ዛሬም እንደትላንቱ በትግሉ አውድማ ላይ ቆሞ እርዱኝ፣ ደግፉኝ፣ ተነሱ እንታገል ይላል ብለዋል።

በዚህ አጋጣሚ ይህን የተሳካ የእራት ምሽት ለማካሄድ የደገፉትንና በቦታው ተገኝተው ትብብራቸውን ሞቅ ባለ ስሜት ለገለጡ ወገኖች አዘጋጆች ከልብ ያመሰገኑ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

ተባብረን ለሕዝባችንና ለሀገራችን እንድረስ!!
በቶሮንቶ የኢሕአፓ ደጋፊዎች